የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ ስምንተኛ ዓመት ቁጥር ፫
አዲስ አበባ ህዳር ፲፩ ቀን ፪ሺ፬ ዓ.ም.

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

18th Year No.3
ADDIS ABABA 21st November 2011

ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፪፻፶፭/፪ሺ፬
የኢትዮጵያ የባሕር ትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ አገልግሎት ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ............
..........................................................ገፅ ፮ሺ፪፻፲፯

## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፶፭/፪ሺ፬

## የኢትዮጵያ የባሕር ትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ አገልግሎት ድርጅትን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፩/፪ሺ፫ አንቀጽ ፭ እና በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ አንቀጽ ፵፯(፩)(ሀ) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ የባሕር ትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ አገልግሎት ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፶፭/፪ሺ፬" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪. መቋቋም

፩/ የኢትዮጵያ የባሕር ትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ አገልግሎት ድርጅት (ከዚህ በኋላ "ድርጅት" እየተባለ የሚጠራ) የመንግስት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

፪/ ድርጅቱ በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ መሠረት ይተዳደራል፡፡

### ፫. ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን

በመንግስት የሚሰየም አካል የድርጅቱ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ይሆናል፡፡

CONTENTS

Regulation No. 255/2011

Ethiopian Shipping and Logistics Services Enterprise Establishment Council of Ministers Regulation............
.......................................................................Page 6217

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION No. 255/2011

## COUNCIL OF MINSTERS REGULATION TO ESTABLISH THE ETHIOPIAN SHIPPING AND LOGISTICS SERVICES ENTERPRISE

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 691/2010 and Article 47(1)(a) of the Public Enterprises Proclamation No. 25/1992.

### 1. Short Title

This Regulation may be cited as the "Ethiopian Shipping and Logistics Services Enterprise Establishment Council of Ministers Regulation No. 255 /2011"

### 2. Establishment

1/ The Ethiopian Shipping and Logistics Services Enterprise (hereinafter the "Enterprise") is hereby established as a public enterprise.

2/ The Enterprise shall be governed by the Public Enterprises Proclamation No. 25/1992.

### 3. Supervising Authority

An organ to be designated by the government shall be the supervising authority of the Enterprise.

ያንዱ ዋጋ
Unit price 3.65

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፹ሺ፩
Negarit Gazeta P.O.box 80,001

፬. **ዋና መስሪያ ቤት**

የድርጅቱ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በማናቸውም ስፍራ ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል፡፡

፭. **ዓላማ**

ድርጅቱ የተቋቋመባቸው ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

፩/ በጠረፍ አካባቢ፣ በአለም ዓቀፍ ባሕሮች እና የሀገር ውስጥ ውሃ ትራንስፖርት አገልግሎት መስጠት፤

፪/ የዕቃ አስተላላፊነት ውክልና፣ የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት፣ የመርከብ ውክልና እና የአየር ውክልና አገልግሎት መስጠት፤

፫/ ለወጪና ገቢ ዕቃዎች የስቴቬዶሪንግ፣ ሾር ሃን ሊግ፣ የደረቅ ወደብ፣ የመጋዘን እና ሌሎች የሎጀስቲክስ አገልግሎቶች መስጠት፤

፬/ የኮንቴይነር ማስተናገጃና ማከማቻ አገልግሎት መስጠት፤

፭/ የወደብ ይዞታዎችን ማልማት፣ ማስተዳደርና አገልግሎት መስጠት፤

፮/ የማሪታይም ዘርፍ የሙያ ክህሎት ማሳደጊያ የሰው ኃይል ልማትና ስልጠና ማዕከል ማቋቋምና ማስተዳደር፤

፯/ የሃገሪቱን የገቢና የወጪ ንግድ ፍላጎት በማጥናት የማሪታይምና ትራንዚት ትራን ስፖርት አገልግሎት አሰጣጥን ብቃት ለማሳ ልበት የሚያስችል የቴክኖሎጂ አቅም ማሳ ደግ፤

፰/ ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ የሆኑ ሥራዎችን ማካሄድ፡፡

፮. **ካፒታል**

ለድርጅቱ የተፈቀደው ካፒታል ብር ፫ቢሊዮን፯፻፷ሚሊዮን(ሦስት ቢሊዮን ሰባት መቶ ስልሳ ሚሊዮን ብር) ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር ፱፻፵ሚሊዮን፯፻፺፱ሺ (ዘጠኝ መቶ አርባ ሚሊዮን ሰባት መቶ ዘጠና ዘጠኝ ሺ ብር) በጥሬ ገንዘብና በአይነት ተከፍሏል፡፡

፯. **ኃላፊነት**

ድርጅቱ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም፡፡

፰. **ድርጅቱ የሚቆይበት ጊዜ**

ድርጅቱ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል፡፡

፱. **የተሻሩ ደንቦች**

የባሕርና ትራንዚት አገልግሎት ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፺/፲፱፻፹፮ እና የደረቅ ወደብ አገልግሎት ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስ ትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፴፮/፲፱፻፺፱ በዚህ ደንብ ተሽረዋል፡፡

4. **Head Office**

The Enterprise shall have its head office in Addis Ababa and may have branch offices elsewhere, as may be necessary.

5. **Objective**

The objective for which the Enterprise is established are:

1/ to render coastal and international marine and internal water transport services;

2/ to render freight forwarding agency, multimodal transport, shipping agency and air agency services;

3/ to provide the services of stevedoring, shore-handling, dry port, warehousing and other logistics services for import and export goods;

4/ to provide container terminal services;

5/ to engage in the development, management and operation of ports;

6/ to establish and run human resources development and training center in the field of maritime profession;

7/ to study the country's import and export trade demand and thereby develop technological capacity in order to render efficient maritime and transit transport services;

8/ to engage in other related activities conducive to the achievement of its objective.

6. **Capital**

The authorized capital of the Enterprise is Birr 3,760, 000,000 (three billion seven hundred sixty million Birr) of which Birr 940,799,000 (nine hundred forty million seven hundred ninety nine thousand Birr) is paid up in cash and in kind.

7. **Liability**

The Enterprise shall not be held liable beyond its total assets.

8. **Duration**

The Enterprise is established for an indefinite duration.

9. **Repealed Regulations**

The Maritime and Transit Service Enterprise Establishment Council of Ministers Regulation No.190/1994 and the Dry Port Service Enterprise Establishment Council of Ministers Regulation No. 136/2007 are hereby repealed.

## ፲. የመብትና ግዴታ መተላለፍ

የኢትዮጵያ ንግድ መርከብ ድርጅት አክስዮን ማህበር፣ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፺/፲፱፻፹፮ ተቋቁሞ የነበረው የባሕርና ትራንዚት አገልግሎት ድርጅት እና በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፴፮/፲፱፻፺፱ ተቋቁሞ የነበረው የደረቅ ወደብ አገልግሎት ድርጅት መብቶችና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ለድርጅቱ ተላልፈዋል።

## ፲፩. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ህዳር ፲፩ ቀን ፪ሺ፬ ዓ.ም

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## 10. Transfer of Right and Obligation

The rights and obligations of Ethiopian Shipping Lines Share Company, the Maritime and Transit Service Enterprise established under the Council of Ministers Regulation No. 190/1994 and the Dry Port Service Enterprise established under the Council of Ministers Regulation No. 136/2007 are hereby transferred to the Enterprise.

## 11. Effective Date

This Regulation shall come into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa, this 21st day of November, 2011.

**MELES ZENAWI**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

፲. **የመብትና ግዴታ መተላለፍ**

የኢትዮጵያ ንግድ መርከብ ድርጅት፣ አክሲዮን ማኅበር፣ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፺/፲፱፻፹፩ ተቋቁሞ የነበረው የባሕርና ትራንዚት አገልግሎት ድርጅትና በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፶፮/፲፱፻፺፱ ተቋቁሞ የነበረው የወደብ አገልግሎት ድርጅት መብቶችና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ለድርጅቱ ተላልፈዋል።

፲፩. **ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ህዳር ፲፬ ቀን ፳፻፬ ዓ.ም

መለስ ዜናዊ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ጠቅላይ ሚኒስትር

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት